# ገዢዎቻችን እነማን ነበሩ?
(ከታሪክ ማኅደር)

**ጌታቸው ኃይሌ**

*መጀመሪያ ደርግ ፥ ቀጥሎ ጎሰኞቹ ወያኔዎች የሀገሪቱን ሥልጣን እስኪያዙበት ዘመን ድረስ ኢትዮጵያን ይገዙ የነበሩት ፥ "እግዚአብሔር የምድር ላይ ክርስቲያናዊት መንግሥቱን እንድንጠብቅለት ኀላፊነት የተጣለብን የዳዊት የሰሎሞን ቤተ ሰብ ነን" በሚሉ ንጉሣዊ ገዢዎች ነበር ። ሦስቱም ገዢዎች (ማለት ፥ ንጉሣዊው ፥ ደርግ ፥ ወያኔ) ሁሉም የሚታሙበት ወንጀል ሲኖራቸው ፥ ከወያኔዎቹ በቀር ማናቸውም ኢትዮጵያን በጎሳ ፖለቲካ አላመሰቃቀሏትም ። በተለየ ዛሬ በአማራነት የሚታማው ንጉሣዊ ቤተሰብ ደጋፊዎቹን የሚመለምለው በታማኝነት ጥቅም ከሚካፈሉ ኢትዮጵያውያን ውስጥ እንጂ ከእገሌ ወገን ብሎ አልነበረም ። ሰሎሞናዊው ቤተ መንግሥት ከየትኛውም ጎሳ የተመለመሉ ችሎታ ያላቸው ጥቅመኞች መዶለቻ እንጂ የጎሳ ወገንተኝነት ቦታ አልነበረም ። መንግሥቱ ግን ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ያቋቋሙት የክርስቲያን ቤተ ሰቦች ስለነበሩ ዋናዎቹና ካህናቱ ሁል ጊዜም ክርስቲያኖች ነበሩ ። የጎሳ ልዩነት ግን ፥ በተለየ በትግሬዎች ፥ በአማሮች ፥ በጉራጌዎች ፥ በሲዳማዎች ፥ በአገዎች ፥ በጋፋቶች ፥ በኦሮሞዎች ፥ መካከል ምን ጊዜም አልነበረም ። ደማቸው ከሁሉም ይጠቅሳል ። ብዙዎች ጎሳዎች የጠፉት ተገድለው ሳይሆን በባህል አማሮችና ኦሮሞዎች ሆነው ነው ። ይኸንን እውነታ በብዙ አጋጣሚ በማስረጃ ተችተነዋል ። ሆኖም ፥ ብዙ ሰዎች ፥ በተለየም የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግምባር (የኦነግ) ሰዎች ፥ የማይናጋ ሃይማኖት-መሰል የታሪክ እምነት ስላላቸው እምነታቸውን የሚያናጋ እውነታው በምንም አነጋገር ፥ በምንም ማስረጃ ቢቀርብላቸው ሊቀበሉት አይፈልጉም ። ትግሉን በፖለቲካ ላይ ሳይሆን ፥ በሌለ ብዙ ዘር ፥ በሌለ አንድ ጎሳ ፥ በሌለ አንድ ባህል ላይ እንዲያተኩር ያደርጋሉ ።*

*የንጉሣዊ ቤተ ሰቦች የሚገዙትና የሚያጋዟቸውን መኳንንት የሚመለምሉት በአገልግሎትና በታማኝነት እንጂ በጎሳ እንዳይደለ የአፄ ቴዎድሮስ ፥ የአፄ ዮሐንስ ፥ የአፄ ምኒልክ ፥ የአፄ ኃይለ ሥላሴ ደም እና የመኳንንቶቻቸው ታሪክ ቢመሰክርም ፥ ብዙ ጊዜ በማስረጃነት የሚጠቀሰው የአፄ ኢዮአስ ማንነት ነው ። ግን የዚህ ንጉሥ ታሪክ የተመዘገበው በግዕዝ ስለሆነ ፥ የንጉሡን የአነሣሥ ታሪክ እንኳን ብዙ ሰው አያውቀውም ። ስለዚህ እውነታው እንዳለ ሆኖ ፥ ዕውቀት ለሚፈልግ ጥቅሙ ስለታየኝ ፥ ከንጉሡ ታሪክ ውስጥ ከመነሻው ላይ ቀንጠብ አድርጌ ለአማርኛ እንዲመች እያደረግሁ ፥ ለጊዜው የማያስፈልጉ መሥመሮችንም እየዘለልኩ እንደሚከተለው ተርጕሜዋለሁ ።*

*የዛሬ ሁለት መቶ አምሳ ስድስት ዓመት የሆነውን ስናጠና ፥ ንጉሥ ሲሞትና ምትኩ አልጋ ሲወርስ ምን እንደሚደረግ ፥ ጸጥታ እንዳይደፈርስ ምን ዓይነት ጥንቃቄ እንደሚወሰድ ፥ መኳንንቱ እነማን እንደነበሩ ፥*

ሥልጣን ከእኛቸው እንዳትወጣ እንዴት ነቅተው እንደሚጠብቁ ፥ ታሪክ ጸሐፊው ከግዕዝ እየወጣ ወደአማርኛ ለመሄድ እንዴት እንደሚገደድ ለማየት አጋጣሚው ዕድል ይሰጠናል ፤

ሰኔ 21 ቀን ፥ ኃሙስ ዕለት [1747 ዓ.ም.] ፥ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ በዓል ዕለት ማለት ነው ፥ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አድያም ሰገድ ኢያሱ አረፈ ። በዚህ ጊዜ (አብራው ትገዛ የነበረችው) እናቱ ንግሥት ብርሃን ሞገሳ እሪ አለች ። "ወዮልኝ ልጄ ፥ ፍቅሬ ሆይ ፤ ወዮልኝ የዓይኔ ብርሃን ሆይ ፤ ወዮልኝ የልቤ ደስታ ሆይ!" እያለች አለቀሰች ። እንዲህ ትል የነበረው ደረቷን እየመታች ፥ የራሷን ጠጉር እየነጨች ፥ ከመሬት እየወደቀች ነበር ። እንዲህም አለች ፤

የላስታን ዓቀበት ያለፈረስ ያለበቅሎ የወጣህ ፤
እንዴት በፈትል ገመድ ታሰረ እግርህ ።
የሄድክ ሆይ ፥ እስከ ምድረ ዋግ ፤
ልታጠፋ ጠላትን (ያንን) ጠባየ <u>ፀዋግ</u> ።
የሄድክ ሆይ ፥ እስከ ምድረ ዶባ ፤
ግብር ልትቀበል ከሕዝቧ ።
የሄድክ ሆይ ፥ እስከ ምድረ ወፍላ ፤
ለመውጋት እስላምና ጋላ ፤
ድንኳንክን የተከልክ በመሃከሏ ።

ደግሞም እንዲህ ትል ነበረ ፤ "እንደዚህ አልጋ ላይ ተጋድመህ ከማይህ ሞቶ መቀበር ይሻለኝ ነበረ ።"

ዘመዶቿ ጩኸቷን በግድ አስጣሏት ። "ከእንገዴህ ወዲያስ የሚሻለው ለእኛም ለዓለምም የሚበጀውን ምክር መመካከር ነው" አሏት ። ከዚያ በኋላ ፥ ንግሥት ምንትዋብ አሳላፊ እሸቴን (ጠርታ) ፤ "ራስ ወልደ ልዑልን ጥራው" አለችው ። ራስ ወልደ ልዑል በታላቅ ግርማ መጣ ። መስቀል ግምብ ወደሚባለው ቤተ መንግሥት ሲገባ ፥ ንጉሥ ኢያሱን አርፎ አገኘው ። ደግሞ ደጅ አዝማች ጌታን ፥ ደጅ አዝማች አውሳብዮስን ፥ ደጅ አዝማች ማሞን አስጠራቻቸው ። መጡና አይተው እንደሞተ ተረዱ ። በእናቱና በዘመዶቹ ማህል ትልቅ ዋይታና ሰቆቃ ሆነ ፤ ልክ (ወንጌላዊው) ዮሐንስና እመቤታችን ማርያም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተሰቀለ ዕለት ዋይታ እንደሆነባቸው ።

በዚህ ጊዜ ፥ ራስ ወልደ ልዑል እኅቱን ንግሥት ብርሃን ሞገሳን እንዲህ ብሎ ጠየቃት ፤ "(ንጉሡ) በሕይወቱ ሳለ ፥ ከሾቱ ልጆቹ ፣ ከአቤቶ ዓፅቁ ፥ ከአቤቶ ኃይሉ ፡ ከአቤቶ ዋዩ አልጋውን የሚወርሰው ማንኛው እንደሆነ ምን ነገር ነገረሽ?" (ዋዩ) የወሎ አሚጠ ጋላ ልጅ ፥ የሉባውና የዱላው እኅት

ከሆነችው ከእመቤት ወቢ የተወለደው ኢዮአስ የተባለው ነው ። ንግሥት ለወልደ ልዑል እንዲህ ብላ መለሰችለት ፤ "ከዳዊት እስከ አሁን እንደነበሩ ንጉሦች አባቶቼና ዘመዶቼ በሞት ከቀደምኩሽ ልጄን ኢዮአስን አንግሺው ፤ ምክንያቱም ያዕቆብ ልጁን ዮሴፍን ይወደው እንደነበረ ፥ ዳዊት ዮናታንን ከአቢሳ አብልጦ ይወደው እንደነበረ ፥  እኔም ከሁለቱ ልጆቼ አብልጬ እወደዋለሁ" ብሎኝ ነበር ። ራስ ወልደ ልዑልና ዘመዶቿ ፤ "ንጉሠ ነገሥት ኢያሱ እንዳለው ይሁን" አሏት ። ሐሳቡን ወደዱት ፤ ምክንያቱም ንጉሣቸው ብቻ ሳይሆን ፥ ሰሎሞን ሠራዊቱ ይወደው እንደነበረ ያፈቅሩት ነበረ ።

ከዚህ በኋላ ፥ ራስ ወዳጄንና ባላምባራስ ዱሪን አስጠራቻቸው ። ይህ ሁሉ ሲሆን ከቤተ መንግሥቱ ውስጥ የሚላላኩ ባለሟሎች ነበሩ ፤ እነሱም የሻለቃ ወልደ ሐና ፥ የሻለቃ አርማስቆ ፥ የሻለቃ ገርቢና ፥ ነጋድራስ ጌርጊስ ነበሩ ። (ነጋድራስ ጌርጊስ) ንግሥት ወለተ ጊዮርጊስ የምታደርገውን እስክታደርግ ድረስ የቤተ መንግሥቱን በሮች በብረት መቀርቀሪያ ዘግቷቸው ነበር ።  በዚያ ጊዜ ንግሥቲቱ አሳላፊ እሸቴን ፥ ራስ ወዳጄ በበቅሎ ቤት ባለበትና እነዚህ ቀደም ብለን የዘረዘርናቸው ባለሟሎች ባሉበት እንዲህ ብሎ እንዲነግራቸው አዘዘችው ፤

> እነሆ ድምፁ በአራቱ መዓዝነ ዓለም ባሉ ሕዝቦችና ነገዶች ዘንድ እንደመብረቅና እንደነጐድጓድ የሚሰማው ፥  የምታፈቅሩት ንጉሣችሁ ኢያሱ አድያም ሰገድ አርፏል ። እንግዴህ ፥ ስለሚነግሥላችሁና እንደ ልጄ እንደ ኢያሱ በየጠባያችሁ ስለሚያሳድራችሁ (ንጉሥ) ምከሩ ። እንዲሁ ስል የልማድ ያህል ተናገርኩ እንጂ ፥ እንደ እውነቱ ከሆነስ እንደልጄ እንደ ኢያሱ የሚሆንስ አይገኝም ።

ለንግሥት ምንትዋብ እንዲህ ሲሉ መልስ ሰጧት ፤

> ንጉሡ በቃሐ በነበርን ጊዜ እንዲህ ሲል አጫውቶናል ፤ "ስሞት ምን ታደርጋላችሁ? መቸም የኖረ ሰው  ሞትን ሳያያት አይቀርም ።" እኛም በአንድ ቃል ፥ "አንተ ከሞትክ እረኛ እንደሌላቸው በጎች እንበተናለን ፤ ልክ መጽሐፉ ፥ እረኛውን እገድለዋለሁ ፤ የበጎች መንጋዎቹም ይበተናሉ እንዳለ" አልነው ። ንጉሥ ኢያሱ ይኸንን ሲሰማ ፥ "እንዲህ ያለ ነገርስ ጥሩ አይደለም ፤ (መጽሐፉ እንደሚለው) ዮዳሔ የሰባት ዓመቱን ልጅ ኢዮአስን እንዳነገሠው እናንተም ልጄን ኢዮአስን  አንግሡት" አለን ።

አሳላፊ እሸቴ ይኸንን ስምቶ ወደንግሥት ብርሃን ሞገሳ ዘንድ ሄዶ ራስ ወዳጄ ፥ ባላምባራስ ዱሪ ፥ የሻለቃ ወልደ ሐና ፥ የሻለቃ አርማስቆ ፥ የሻለቃ ገርቢ የነገሩትን ሁሉ ነገራት ። ይኸን ሲነግራት ፥ "ለኔም የነገረኝ ይኸንኑ ነው ፤ ያዘዛችሁን ፈጽሙ ። እኔ ግን ከአሁን ወዲያ  የሰማዩን መንግሥት እንጂ የዚህን የኃላፊ ዓለም መንግሥት አልፈልግም አለች ብለህ ንገራቸው" ብላ አሳላፊ እሸቴን አዘዘችው ። ሄዶ ለላኩት ነገራቸው ። ሰምተው ፥ "መንግሥቱን እሊቃለሁ ፤ በዚህ ዓለም አልኖርም"

በማለቷ ሲተክዙ ፥ ኢዮአስን ስለማንገሥ ጉዳይ ንጉሠ ነገሥት ኢያሱ ቀደም ብሎ የነገራቸው ከእሷ ቃል ጋር አንድ በመሆኑ ተደሰቱ ። ንግሥት ወለተ ጊዮርጊስን ግን መንግሥት ያለ እሷ ስለማይጸና ፥ እንዳይለቋት ፥ አቤቶ ኢዮአስን እንዲያነግሡ ሁሉም በኵርዓተ ርእሱ ሥዕል ተማማሉ ።

ከዚህ በኋላ መኳንንቱንና የፍርድ ሊቃውንቱን ሁሉ ጠሩና እያንዳንዱን ለየብቻቸው አስማሏቸው ። መኳንንቱና ሊቃውንቱ ደግሞ ተራቸውን ዘመዶቿን እነራስ ወልደ ልዑልን ፥ ደጅ አዝማች ጌታን ፥ ደጅ አዝማች አውሳብዮስን ፥ ደጅ አዝማች ማሞን ፥ አሳላፊ እሸቴን ፥ የሻለቃ ክንፉን ፥ አቤቶ የማርያም ባርያን ፥ አቤቶ ወልደ ሚካኤልን ፥ ሌሎችንም በቤተ መንግሥት የሚኖሩ የቅርብ ዘመዶቿን አስማሏቸው ። ንግሥት ብርሃን ሞገሳ ገዳም እንዳትገባ እንዲጠብቋት አደራ አሏቸው ።

መኳንንቱና ዘመዶቿ በመሐላ አንድ ከሆኑ በኋላ ፥ ባላምባራስ ዱሪንና ዞጌ ያቦ ባርያን ሕፃኑን ኢዮአስን ከእናቱና ከአሳዳጊው ጋር በጥድፊያ እንዲያመጡት ተወልዶ በካህናቷ ጸሎት ወደ አደገባት ደብረ ፀሐይ ወደምትባለው ወደ ታቦተ ቊስቋም ላኳቸው ። አምጥተው ከመሰሪ አስገቡት ። ከዚያ በኋላ ከመሰሪ አውጥተው ወደ መናገሻ ግምብ አውጥተው ከፍ ካለ የወርቅ ዙፋን ላይ አስቀመጡት ፤ ዓይን የሚማርክ የመንግሥት ልብስ አለበሱት ፤ ዘውድ ጠባቂው ነጋድራስ ጌርጊስ ዘውዱን ይዞ መጣና እንደ ሕጉና እንደሥርዓቱ አነገሡት ።

ከዚያ በኋላ አሳላፊ እሸቴ መኳንንቱን ፥ ሊቃውንቱን ፥ አዛዦቹን የየቤተ ክርስቲያኖቹን ሊቃውንት የጨዋ ልጆችን ሁሉ መጥተው እጅ እንዲነሡ ጠራቸው ። እጅ ነሡ ፤ "ንጉሥ ሆይ ፥ ለዘላለም ኑር" አሉ ። ደጃዝማች ጌታ ከመኳንንቱና ከሊቃውንቱ ጋር ወጥቶ ፥ ከዓዋጅ መንገሪያው አደባባይ ማህል ቆመ ። ሕግ ጠባቂዎች ሲመጡ እንዲህ የሚል ዓዋጅ ተነገረ ፤

> እነሆ ንጉሠ ነገሥት ኢያሱ አርፏል ፤ በሱ ቦታ ልጁ ንጉሠ ነገሥት ኢዮአስ ነግሧል ፤
> የሞትንም እኛ ነን ፤ያለነውም እኛ ነን ፤ [ስለ ሞትን እንዘን ፤ ስለነገሥን እንደሰት ።]

ዓርብ ዕለት በጠዋት መኳንንቱ ሊቃውንቱ ሠራዊቱ ሴት ወይዘሮዎቹ እና የግቢው ሰው ሁሉ ተሰብስበው ከፍ ያለ ልቅሶ አለቀሱ ። ከዚያ ወደአደባባይ ወጥተው ፡ የሞተውን ንጉሥ ምስል ሠሩ ። ወምበዴ የሚባለውን በቅሎውና ሎላ እና ሳልዳ የሚባሉትን ሁለቱን ፈረሶቹን በንጉሥ ልብስ አስጌጧቸው ። ትልቁና ትንሹ ሁለቱ ጃንጥላዎች ተያዙ ። አንድ አምበል ከፈረስ ላይ ወጣ ። ሰንደቅና ነጋሪት ከሌሎች ሕግ ጠባቂዎች ጋር ወጡ ። መጀመሪያ ነፍጠኛ እመካበቢያ ድረስ ወጣ ፤ ቀጥሎ ከምስሉ ቀደም ብሎ ሰይፈ እጃግሬ ወጣ ፤ ከምስሉ ከተል ብሎ ጋሻ እጃግሬ ወጣ ። ከዚያ መኳንንቱ የኀዘን ልብስ ለብሰው ተከተሉ ። በማህላቸው ደጅ አዝማች ጌታ ፥ ደጅ አዝማች አውሳብዮስ ፥ ደጅ አዝማች ማሞ ፥ አሳላፊ እሸቴ አሉ ። በወይዛዝርቱና በደረባ ቤት ማህል ከፍ ያለ ጩኸት ሆነ ። የንጉሠ ነገሥቱ እናት ይቴጌ ምንትዋብ ከእናቷ ከወይዘሮ እንኰየ ፥ ከብዙ የሴት

ዘመዶቿ ፥ ከአምቻዎቿ ፥ ከይቴ አግሮዶች ጋር ኀዘን ጸናባት ። በኀዘን ዜማ (በአማርኛ) እንዲህ እያሉ አለቀሱ ፤

አያ በሰቀላህ ወህ ሞላ ፤ በሰቀላህ ወህ ሞላ ።
የተራብ ዘመድ እንዳይበላ ።
ወይ እርሱ ሳለ ቀሊል ኢያሱ ለጋሱ ።
አንተ የወፍላ ንጉሡ ።
እንዘን ፥ አብረን አድገናል ፤
አብረን እናልቅስ ፤ አብረን በልተናል ።
ከዝያ ሰው ፥ የጌታ ባልንጀራ ፤
ሞቴን ያድርገው ካንተ ጋራ ።
ካንተ ጋራ ሞቴን ያድርገው ።

ደግሞ የንጉሥ ኢያሱ ሎሌዎች (በአማርኛ) አለቀሱ ፤
ተያይዘው አንገት ላንገት ፤
ቢሞትባቸው ድንገት ፤
"አለ ፥ አለ" ሲሉት ።
የለመዱ ሹመት ፤
ያልተሾሙ በከብት ፤
ከፍ ፥ ከፍ ያሉም በጕልት ።

ይኸንን ለቅሶ ያየና የሰማ ከጐንደር እስከ ምድር ወሰን ፥ እስላም ፥ አምሐራ ፥ ቅማንት ፤ ፈላሻ ፥ ወታደር በጋሻ ፤ መነኵሴ በዋሻ ፤ ነጋዴ ሰው ሳይሻ ፤ የሚሄድ በጣቻ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ ።

ቅዳሜ ዕለት ሰኔ 23 ቀን ደጃዝማች ወረኛ ጐንደር ገባ ፤ ንጉሡ ነገሥት ኢዮአስና ንግሥት ምንትዋብ ከመኳንንቱ ፥ ከሴት ወዛዝርቱ ፥ ከሌሎቹም ሠራዊት ፥ ማለት ፥ ከኒሳ ፥ ትግሬ ፥ ላስቴ ፥ እኛግሬ ፥ ጋሻ እኛግሬ ፥ ግምጃ ቤት ፥ ሰይፍ እኛግሬ ጋር በመሰሪ መከታ ነበሩ ። ካለፈው የሚበልጥ ትልቅ ለቅሶ ሆነ ። ባለሚሎቹ የሻለቃ ወልደ ሐና ፥ የሻለቃ አርማስቆ ፥ የሻለቃ ገርቢ ፥ የሻለቃ ቶማ ፥ የሻለቃ መርዱ ትግሬ ፥ የሻለቃ ፋሬስ ክንፉ ፥ የሻለቃ ከብቴ--ትርፍ ስሙ በሬ በላ--አሳላፊ እሸቴ ፥ አሳላፊ ክንፉ ፥ አሳላፊ ገብረ መስቀል ፥ አሳላፊ ተስፋ ፥ አሳላፊ ላፍቶ ጎቴ አውዶክዮስ ፥ አሳላፊ ያሬድ እሸቴ ማሞ ፥ አቤቶ የማርያም ባርያ ፥ ዞጌ ያቦ ባርያ ፥ ቢሶሪስ ገብሩ ፥ አቤቶ ወልደ ሚካኤል ፥ እማያ ኮቾ ፥ ግራና ቀኝ ቆመው (በአማርኛ) እንዲህ እያሉ በኀዘን ዜማ አለቀሱ ፤

እንዴት ዋላችሁ ፤ ሳትዋጉ ድል ተነሣችህ ።

በጎም አልዋልነ ፤ ሳንዋጋ ድል ተነሣነ ።

በዚያ ጊዜ ግማሹ ጋሻና ጦር ይዟል ፤ ግማሹ ሰይፍ ይመዛል ፤ ግማሹ ጠመንጃ ያንጐደጕዳል ፤ ግማሹ ቀስት ይወጥራል ፤ ግማሹ ፈረሱን የጦር ልብስ እያለበሰ ጎምለል ጎምለል ይላል ። ደጃዝማች ወረኛ ይኸን ሁሉ ሲያይ ከተቀመጠበት የሰቅሰቅ አሸዋ ብድግ ብሎ አብሯቸው አለቀሰ ። የንጉሠ ነገሥት ኢያሱ ወዳጅ ስለነበረ ፥ ከዳሞትና ከጃዊ ጋር ሆኖ ኀዘን በረታበት ። ዳሞትና ጃዊ ጋላና መጫ ናቸው ።

ሰኞ ዕለት ፥ ሰኔ 25 ቀን ፥ ንጉሡ አጃሌ ግምብ ከሚባለው ቤተ መንግሥት ገባ ። አቡነ ዮሐንስ ፥ እጨጌ ኤዎስጣቴዎስ ፥ የደብረ ሊባኖስ ካህናት በአንድነት አብረዋቸው ሲገቡ ፥ ንጉሥ ኢዮአስን ፥ አጃሌ ግምብ ውስጥ ከንግሥት ወለተ ጊዮርጊስ ፥ ከመኳንንቱ ፥ ከፍርድ ሊቃውንቱ ፥ ከዓቃቤ ሰዓት ኢዮብ ጋራ ሆነው አገኟቸው ። ጳጳሱ አቡነ ዮሐንስ ፥ "ዘውዱን ሜሮን እንድቀባው አምጡ" አሉ ። ሜሮን ንጉሥ የሚቀባበት ነው ። ነጋድ እራስ ጌርጊስ ዘውዱን አመጣ ። ጳጳሱ ንጉሥ ኢዮአስንና ዘውዱን በመስቀል ምልክት ቀባቸው ። አክሊሉን ራሱ ላይ ደፍቶለት ለንግሥ የሚገባውን ጸሎት ጸለየ ።

ማብራሪያ ፤

1. ንግሥት ብርሃን ሞገሳ ፥ ንግሥት ወለተ ጊዮርጊስ ፥ ንግሥት ምንትዋብ የአንድ ሰው የዘውድ ስም ፥ የክርስትና ስም ፥ የዓለም ስም ናቸው ። አገር የሚገዙት በሥርዓት ዘውድ የጫኑ ንጉሥና ንግሥት ነበሩ ፤ ንግሥት የምትሆነው የንጉሡ ሚስት ብትሆንም ፥ የንጉሡ እናት የምትሆንበት አጋጣሚም ይኖራል ።
2. "ጠባየ ፀዋግ" ማለት "ጠባየ ጠማማ" ማለት ነው ፤ እቦታው ያልተረጐምኩት ፥ ግጥሙን እንዳያበላሽ ነው ።
3. "ኵርዓተ ርእሱ" ሥዕል የሚባለው ኢየሱስ አይሁድ የሾህ አክሊል ጭነውበት የተሣለው ሥዕል ነው ። ረጅም ታሪክ አለው ።
4. "የፍርድ ሊቃውንት" የሚባሉት በዳኝነት ጊዜ ፍርዱ ሕግ የተመረኰዘ እንደሆነ የሚያረጋግጡ የሕግ ተርጓሚዎች ናቸው ።
5. "ሕግ ጠባቂዎች" የቤተ መንግሥቱ ሥርዓት የሚቆጣጠሩ ፥ የሕጉ ቅጂ በእጃቸው ያለ ሊቃውንት ናቸው ።
6. "ታቦተ ቍስቋም" ጎንደር ከተማ ውስጥ ንግሥቲቱ (ምንትዋብ) ያሠራችው ቤተ ክርስቲያን ነው ።
7. "መሰሪ" የአዳራሹ ስም ነው ።
8. ታሪክ ጸሐፊዎቹ የሃይማኖት መጻሕፍት ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ምሳሌ መጥቀስ ይቀናቸዋል ።

9. "ዳሞትና ጃዊ ጋላና መጫ ናቸው" የሚለው አነጋገር የሚያመለክተው ፥ ኦሮምኛ የሚናገረውን ሁሉ ጋላ ይሉት እንዳልነበረ ነው ፤ ምክንያቱም ጃዊም መጫም ቋንቋቸው ኦሮምኛ ነው ።

10. ዘር የትም መሬት ላይ ቢዘራ ምርቱ ዘሩን እንጂ መሬቱን እንደማይመስል ፥ ንጉሡ ከየሴቱ የሚወልዳቸው ልጆች ሁሉ ንጉሥ ለመሆን የሚበቁ የሰሎሞን ዘር ነበሩ ።

11. የደብረ ሊባኖስ መነኮሳት ከንግሡ በዓል ላይ የተገኙት ለበዓሉ ሲባል ከሸዋ ድረስ መጥተው አይደለም ። አፄ ሱስንዮስ ካቶሊክ ሲሆን ደብረ ሊባኖስን አዘዞ (ጐንደር አጠገብ) አዛውሯት ነበርና ካህናቱ የመጡት ከአዘዞ ነበር ።